## የዘረኝነት ጣጣ

09/16/2016 በርሀ ሃጎስ( SEGUD 50)

ብዙ አገሮች የነበረውን አሮጌ መተሳሰር(ቦንድ) በማፍረስ የተመሰረቱ ናቸው።የሰው ልጆች እንደ ቤተ-ሰብ,አከባቢ(ክላን) ቤተ-ክርስትያን,መስግድ የመሳሰላ ያስተሳስራቸው የነበረ ቦታ ትቶው ከቦታ-ቦታ ጥቅማ-ጥቅም ፍለጋ መራራጥ ጀመሩ። ኑሮውን ማሻሻል ቀጠለ።ትናንሽ ሽቀጣ ሽቀጥ ተፋፋመ።ውድድር(ኮምፒተሽን) ተጀመረ።

ግና በአከባቢውን ያገኘው የነበረ መተሳሰር በማጣቱ ባዶነት ተሰማው።ያጋጠመውን የባዶነት ክፍተት ለሞምላት ደግሞ,. ቋንቋውን ወደሚናገሩ,ባህሉ,ሃይማነቱ ወዘተ ወደሚመሳሰለው ተጠጋ።ጥቅሙ ለመጠበቅ በማለት ዘሬ ከሚላቸው ወገኖች ይወግናል።ተከትሎ ብሄረ-ሰብ ይጠነሰሳል።ብሄር-ዘር ወዘተ በማለት እንደ ሁነታው ስሙም ይቀያየራል።ዘረኝነት ኣብዛኛው ግዜ ሁለት ስለት ያለው ቢላዋ ይዞ ብቅ ይላል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተወሰኑ የምራባውያን ሙሁራን ዓለም አቀፋዊ ንግድ ከተስፋፋ ሁሉ የሰው ልጅ የጋራ እድገት ሊያመጣ ይችላል ብሎው የሚያስቡ ነበሩ።ይህ ኣመለካከት ሁሉን የሰው ልጅ ይጠቀማል:ሁሉ ከተጠቀመ ደግሞ ዓለም በሞላ ሰላም ይሆናል ብሎው የሚያምኑ ግሎባላዘሽን የሚሎውን ኣመለካከት የሚያራምዱ ናቸው።ሌሎች ግራ ዘመም ኣመለካከት የነበራቸው ደግሞ ግሎባላዘሽን ስራ ላይ ሊዉል የሚችሎው ዓለም በኮምኒስት ስርዓት ማህበር ስትመራ ብቻ ነው ይላሉ።ኮምኒስት ኣመለካከት ያላቸው ሙሁራን ደግሞ ዓለም በኮሙኒስት ከተመራች የግለ-ሰብ መብትንና ጥቅም ስለሚጠበቅ በብሄሮች መሃከል የነበረ ችግሮች ጠፍቶ የሰው ልጅ በመደብ ጀርባ ይተባበራል ይላሉ።ዓለም በሰራተኛ ስትመራ የዓለም ሰራተኛ ይተባበራል ብሎው ነበር።በዚህ መሰረት የሰው ልጅ በዘር በቋንቋ :በሃይማኖት ወዘተ የነበረው ልዩነት ይጠፋል ብሎው ነበር።

በመጀመርያ 20ኛው ክፍለ-ዘመን ግን ብዙ ህዝቦች በግፍ ተላልቀዋል:ፈልሰዋል፡ተፋናቅለዋል፡ተገፍተዋል።በተለይ ጸረ ኣናሳ ብሄራት(ማይኖሪቲ) በሚሉዋቸው ያተኮረ ጥፋት ተስርተዋል።በሃይል ከኣንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተሰደዋል።ብዙ ህዝብ ጠፍተዋል(ጀኖሳይድ) ወይ ዘር ማጽዳት ተፈጽመዋል። የቋንቋና የዘር ማጽዳት(እትኒክ ክሊንዚ) ተፈጽመዋል።

ባለፈው 20ኛው ክፍለ-ዘመን ብዙ ግፍና መከራ እንደነበር ብዙ ማስረጃ ኣያስፈልገንም።ብዙ ዘር ኣብሮ ይኖርባት የነበረው ባልካን ተብሎ በሚጠራ ቦታ እስከ ቅርብ ግዜ ብዙ መፈናቀልና መጣፋት ኣይተናል።

ቀደም ብሎ በመውደቅ የነበረ ኦቶማን ግዛት የሚባሎው ሕብረ-ቤራዊ ኣገር ለመፍጠር ብዙ ግፎችና የእርስ-በርስ ውግያ ኣስከትለዋል።ኣንዱ ዘር በኣንዱ ዘር ተላልቀዋል።እልክ ኣስጨርሽና መተላለቅ ተፈጽመዋል።ቡልጋርያ፡ግሪክ እንዲሁም ሰርብያውያን ብዙ ደም ፈሰዋል።

ቦልካን ጦርነት ተብሎ በሚጠራ የ1912-13 የዘር ጦርነት 500 000 የሚደርሱ ሰዎች ወደዱም ጠሉም ከነበሩበት መሬት ተፈናቅለዋል።የእስላምና ኣማኞች ከቡልጋርያ፡ግሪክና ሰርብያ ከሚኞጣጠሩት ቦታ ተባርረው ወደ መቅዶንያ ሰፍረዋል።እንዲሁም መቅዶንያ ውስጥ ይነሩ የነበሩ ግሪክ ሰርብያ፡ቡልጋርያ ይኖሩበት ከነበሩ ቦታ ተባርረዋል።

ኣንደኛ ዓለም ጦርነት ባስከተለው ሚሊዮን ህዝብ ከኣንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተፈናቅለዋል።በኦተማን ግዛት ይነሩ የነበሩ ኣርመናውያን ተገድለዋል።የዘር ማጽዳት(ጀኖሳይድ)እስከ ኣለንበት ዘመን መፍትሄ ኣልተገኘለትም።

በ1919 ግሪክ ቱርኪን በመውረር እስከ ኮንስታንትኖብል ማስፋፋት ጀመሩ።ሁሉ ገጠሮች ማቃጠል ተያያዙበት።በሌላ በኩል ደግሞ ቱርካውያን ሃይላቸው በመሰባሰብ መልሶ ማጥቃት በማድረግ ግሪኮችን ጨፈጨፉ።በሁለቱ ኣገሮች ዘር ማጽዳት ኣድርገዋል።

በ1923 የላውሳነ(Lausanne)ዉል የሚል ስምምነት የሰው ልጅ ወደየዘሩ በኣግባብ የመመለስ በሚሎው መሰረት ከቱርኪ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ ተባርረዋል.እንዲሁም ከግሪክ 400 000 ህዝብ ወጥተዋል።የግርክ ተወላጆች ወደ ግሪክ ሲባረሩ፡የቱሩክ ተወላጆች ወደ ቱሩኪ ቢመለሱም እስልምና እምነት የነበራቸው የግሪክ ተወላዶችም ሳይቀሩ ወደ ቱርክ ተባርረዋል።

የሃፕስቡርግስና ሮማኖው ግዛት ደግሞ በዘር የተበጣጠሱ ኣገሮች ሆኑ።60 ሚሊዮን ከሚሆኑ የመካከልንና የምብራቅ ኢሮፓ ህዝቦች 25 ሚሊዮኖቹ ኣናሳ ብሄር ሁነዋል።ብዙሃኑ(ማጆርቲ) ውህዳኑን(ማይኖሪቱን) ሊያስጠግዋቸው ወይም ሊያቅፍዋቸው ኣልቻሉም።ኣናሳው ብሄርም ተባብሮው መኖር ኣልሞከሩም።ኣልፈለጉምም።ሁሉ ግዜ ብዙሃኑ ኣናሳውን ጨቑኖ መኖር ይፈልጋል። ኣናሳውም ደግሞ ኣልጨቐንም በማለት መገንጠል ይመርጣል።ኣስተዳደሩ ሁሉ ግዜ የብዙሃኑን ቋንቋ ተናጋሪውን ይቐጣጠረዋል። ኣናሳ ቋንቋ ተናጋሪ ከኣንዳንድ ጥቅማጥቅሞች ይወገዳል።ብሄራዊ ኣድልዎ ይፈጠራል።ግጭት ይጀመራል።ቀጥሎ መጣላት፡ መጋጨት፡መገነጣጠል፡ያስከትላል።የዘር ማንነት በትእግስትና በጥበብ ካልተያዘ እጂግ ኣደገኛ ወደ ሆነው የዘር መጠፋፋት ሊያስከትል ይችላል።

ኣይሁዳውያን ኣብዛኛው መካከለኛው ኢሮፐ በንግድ በልጠው ሂደው ነበሩ።በተለይ የራሳቸው ኣገር ላነበራቸው ኣይሁዳውያን የዜጋ መብት(ሲብል ራይት) ተፈቅድላቸው ስለነበር በትምህርት እየላቁ ስለ ነበሩ በህግ :በክምና ጠቅላላ ዶክቶሮችንና ጠበቆች ሆኑ።ግን እንደገና ኣይሁዶች የነበራቸውን መብት ተነፈጉ።የተሰጣቸውን መብት ተቀሙ።ኣይሁዳውያን ከፍተኛ ትምህርት ቤት እንዳይማሩ ተደረገ። ጀርመናዊነት የናዚ ስሜት በ1933 ዓ/ም የኣይሁዳውያን እድገት ተቀናቃኝ ሁኖ ብቅ ማለት ጀመረ።የ2ኛ የዓለም ጦርነት ግዜ የናዚ ርጂም ኣይሁዶችን ማጥፋት ጀመሩ።በጀርመን የነበሩ ብቻ ሳይሆን ፖላንድ፡ቸኮዝላቫኪያ የነበሩትን

ኣይሁዶችም ጭምር እንጂ።በየኣከባቢው ይኖሩ የነበሩትን ኣናሳ የጀርመን ዘር በመጣናከር በኣይሁዶች መፍጀች ኣስተባበሩዋቸው። የዘር ጥላቻ ተስፋፋ።የሮማንያ ርጂም ከናዚ ርጂም ትእዛዝ ሳይጠብቁ ራሳቸው ኣይሁዶችን ፈጁ።እንዲሁም የክሮስያ ርጂም የራሱን ኣይሁዶች ብቻ ሳይሆን የሮማንያን የሰርብያን ኣይሁዶች ጭምር ፈጀ።

ኣብዛኛው ግዜ ዘረኝነት የሚመነጨው የኣናሳ ብሄረ-ሰብ ኣባላት በማንኛውም መንገድ በጥቅም በኤኮኖሚ ከሌሎች ዘሮች በተለይ ከብዙሃን ከሚባሉ በልጦ ካደገ የበላይነት ከያዘ፡የብዙሃኑ ቤተሰብ ወገን ደግሞ ተበለጥን ወይ ተጎዳን ብሎ ተቃውሞውን ሲያነሳ ነው።ብዙሃን ነን የሚሉ ብሄረሰብ  በኣናሳ  በመበለጡ ስሜት(ቅናት) ያሳድራሉ።ኣናሳው ደግሞ በአልሞት-ባይ-ተጋዳይ መንፈስ ለሥልጣቸው ሲሉ አገሪቱን ገደል ውስጥ ወደሚያስገባ የውጥረት፣ የትርምስና የውድመት ይዞታ ላይ ጎትተው ከመውሰድ ወደ-ኋላ ስለማይሉ፣ የትግሉን መራርነትና የሚያስከፍለውን ከባድ መስዋዕትነት በቀላሉ መገመት አያስፈልግም። ብዙ ግዜ በገጠር የነበረ ዘር በከተሜው እየተዋጠ ሲመጣ የዘር ፉክክር ያስከትላል።ኣንዳንድ ግዜ ዘሮችን በመደባልቅ መፍትሄ መፈለግ ይሞክራሉ።ከድሃ ኣከባቢ  ወደ ሃፍታም  ኣከባቢ በማንቀሳቀስ መፍቴ መፈላለግ ያደርጋሉ።ለምሳሌ እኩል ሚሊዮን ፖላንዳውያን ወደ ኢንግላንድ 200 000 ወደ ኣይርላንድ ተዛውረዋል።ከኣንድ ኣከባቢ ወደ ኣንድ ኣከባቢ በማዛወር በሂደት ተመሳስሎው እንዲኖሩ ተደርገዋል።

ዘረኝነት ከሃይማኖት የሚያያይዙ ሃይሎች ደግሞ ኣሉ።የእስልምና ኣማኞች ለብቻቸው ቦታ ይሰጡ ብሎው ያምናሉ።ሌላ ቀርቶ ኣንድ-ኣንድ የኢሮፓ ማሕበር ኣባላት ቱርኪ ወደ ኢሮፓ ማህበር በኣባልነት ኣንቀበላትም ምክንያቱ የእስልምና ተከታይ ኣገር ናት ይላሉ።

ዘረኝነት በቀጥታ ዘመናውነት(ሞደርናይዘሽን)የወለዶው ነው።ኣንዳ-ኣንድ ኣገሮች የዘር(እትኒክ) ችግር ለግዜው ሊሆን ብችልም በኣውቶኖሚ፡የራስህን እድል በራስህን የመወሰን፡(ሰልፍዲተርሚነሽን) ከዋናው (ካለው) መንግስት ተስማምቶው በሰላም የሚኖሩ ኣሉ።ምሳሌ፡ካታላንስ(Catalans)ከእስፓይን፡ፍለምሽ (Flemish)ከበልጅም፡እንዲሁም እስኮች(Scots) ከትልቅዋብሪተይን ወዘተ። በሰላም ኣብሮው ይኖራሉ።

በማደግ ላይ ያሉት ኣገሮች በተለይ በቋንቋ ቢካለሉም ግጭቱ ሊቆም ኣይችልም።ግጭቱ ኣድጎ ከመስመር ካለፈ ግን ወደ ከፋ እልቂት ደርሶ መፍትሄ ወደማይገኝለት እልቂት ሊያመራ ይችላል።ቋንቋን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች በቶሎ ካልተገቱ አሰቃቂ የእርስ- በርስ ትርምስን ሊያስከትሉ መቻላቸው ታሪክ ያሳየናል።

ይህን ሁሉ ጣጣ የሚያመጡት በጣት የሚቆጠሩ ምሁራን ናቸው።የተቖጡ።ኣብዛኛው ግዜ እጂግ ተስፋ የቆረጡት ምሑራን የሚያቀጣጥሉት እሳት ነው(The behavior of elites is cynical and opportunistic);እኛ ካልገዛን ዓለም ትጥፋ የሚሉት ፍጡሮች(ዓወት ወይ ሞት) የዜሮ- ድምር ጨዋታ (bloody zero-sum struggle in which everything is at stake and no one can afford to lose) ለሰፊ ህዝብ ሳይሆን ለራሳቸውና ለጠባብ ቤተሰባቸው ብቻ ለመጥቀም ነው። ካላሸነፉ አገርም ህዝብም ቢጠፋ ደንታ የላቸውም።ተራ ህዝቡ የነዚህ ሃይሎች ኣገልጋይ ብቻ ናቸው።Ordinary people are not truly citizens but client of powerful local bosses; who are themselves the clients of still more powerful patrons ።በተለይ ባለንበት ዘመን እጂግ ፈጣን የሆነ ሶሻል መድያ በመጠቀም ህዝብ በህዝብ ላይ ከማጫረስ ወደኋላ የማይሉ እንደሆኑ ዛሬ በኣገራችን ምልክቶች እያየን ነው።

ስለ የፖለቲካ ማንነት--ሙሁራን ሁለት የተለያየ መፍትሄ ሃሳብ ያቀርባሉ።በኣንድ በኩል ኣንድነታውያን ሃይል የሚባሉ፡በኣንድ ሃገር የሚኖር ሁሉ ማለት ሃይማኖቱ፡ቋንቋው፡ዘሩ የተለየየ ቢሆንም የዜግነት መብቱ ተጠብቆ፡በእኩልነት ተከባብሮ፡በጋራ ኣንድነትን ጠብቆ መኖር የበለጠ የጋራ ጥቅም ይኖሮዋል ይላሉ።የኣንድ ኣገር ዜጋ ይሆናል ይላሉ።የዚህ ተምሳሌ ኣሜሪካ ናት። የኣንድነት ሃይል ይባላሉ።ይህ ኣመለካከት ያላቸው ሙሁራን መገንጠልን የጠባቦች ኣመለካከት ነው ብሎው ሌላ የመፍትሄ ኣማራጭ ኣይቀበሉም።

በሌላ በኩል ደግሞ የማንነት ዋና መሰረት መገንጠል ነው ይላሉ።ኣገር የሚሉት ኣንድ ልማድ፡ኣንድ ቋንቋ፡ኣንድ እምነት እና ከኣንድ የዘር ግንድ ወይ ትውልድ የሚመሰረት ነው ይሉናል።ይህንን ኢሮፓውያን ሲተገብሩት የነበረ ቢሆንም ኣሜሪካም እስከ ቅርብ ግዜ ስገለገሉበት ነበሩ።በብሄሮችን መገንጠል እንደ መፍትሄ የሚያስቀድሙ ሙሁራን ደግሞ፡ኣንድነታውያንን የትምክህት ቋት ናቸው ብሎው ይኮኑናቸዋል።ኣማራጭ ሃሳብ ከራሳቸው ጥቅም ስለሚያዩት ኣማራጭ ሃሳብ ኣይቀበሉም።

ኣሜሪካ ለብዙ ዘመን ዘራቸው እንግሊዝ፡ሃይማኖት ፕርቲስታንት፡የሆኑ ነጮች፡በተለይ ከስሜን ኢሮፕ የመጡ ናቸው እውነተኛ ኣሜሪካውያን ብሎው እስከ 1965 ዓ፡ም/ኢ ያምኑ ነበር።በ1965 ዓ፡ም/ኢ የሜሪካ ህግ ተሻሽለዋል።ነጭ ብቻ ነው እውነተኛ ኣሜሪካዊ ዜጋ የሚሎው ተሽረዋል።

በብሄር የሚያምኑ ሙሁራን(ብሄራውያን) በዘር ትውልድ ሲወድ-ሲዋረድ የነበረ ቤተሰብ ነን፡በደም የተሳሰርን ነን ወይም በኣንድ ቃል "እኛ" ይላሉ።ከነሱ ቋንቋ ያልወጣ "እነሱ" ይላሉ።ተከትሎው የራሳቸው ብሄር (ሃገር) ይመሰርታሉ።ምዕራብ ኢሮፓ ብሄረተኝነት ኣያጠቃቸውም ይባላል።ወደ ምስራቅ ኢሮፓ በተጠጋህ ቁጥር ጠባብ ብሄረተኝነት እየከረረ ይሄዳል።ቀደም ብሎው የተፈጠሩ ኢሮፕያን ኣገሮች እንደ ኢንግላን፡ፈረንሳይ፡ፖርቱጋል፡እስፓይንና ስዊድን የመሰሉ ኣገሮች ዘረኝነት ኣያጠቃቸውም። ምክንያቱም የብሄር ጥላቻ ሳያድግ ኣገር (ነሺን እስቴትስ) ገንብተዋል።የብሄር ቅራኔ ያልበዛበት ዋና ምክንያት ለብዙ ግዜ የባህልን ተመሳሳይነት የሰሻል መቀራረብ ስለነበራቸው ነው።ለብዙ ግዜ የተሳሰረ ባህልንና ልማድ መቀራረብ ስለነበራቸው ነው።

መካከለኛው ኢሮፕ ጣልያንና ጀርመን እስከ 1860-1870 ተበታትነው ይነሩ የነብሩትን በየቋንቋቸው ተሰባስበው የራሳቸውን ሃገር መሰረቱ።በጣልያን ኣከባቢ የነበሩትን ጀርመናውያን ወደጀርመን፡በጀርመን ይኖሩ የነበሩ ኢጣልያኖች ደግሞ ወደ ጣልያን ተሰባስቦው የየራሳቸው ኣገር መሰረቱ።

መፍትሄ ያልተገኘበት የቋንቋ ግጭት-ከየትኛውም ኣገር ወደ ኣሜሪካ ተሰዶ የገባ ሰው በኣንደኛው ወይም በሁለተኛ ትውልድ የኣሜሪካን ባህልንና ልማድ ተቀብሎ በማንኛውም መልክ ከሃገሪቱን ህዝብ ተመሳስሎ ይኖራል።የኣሜሪካን ህግና ባህል ተቀብሎ በሰላም ይኖራል።የራሱ ቋንቋ የመናገር መብቱ ይጠበቃል።በኣሜሪካ ውስጥ የራሳቸው ባህል ያሳደጉም ኣሉ።ለምሳሌ እስፓንሽ ወዘተ።በቋንቋ ግጭት ግን ብዙ ኣይታይም።ሌላ ቀርቶ በካናዳ (ኮበክ) የሚኖሩ ፈረንሳዮች በኣገራቸው ከናዳ የብሄር ችግር ይነሳል። ኣልፎኣልፎም ግጭት ይታያል።ከካናዳ ተሰደው ወደ ኣሜሪካ ሂደው ግን በሰላም ይኖራሉ።ከመቅርብ(መረኮና ቱኒዝያ) ተሰደው ብዙ ዜጋ ፈረንሳይ በሰላም ይኖራሉ።እንዲሁም ከላይ እንደ ጠቀስኩት ከፖላንድ ተሰደው እንግላንድንንና ኣየርላንድ በሰላም ኢየነሩ ነው።ይህ የሚያሳየው ብሄርተኝነት የኔ ናት በምትላት ቦታ ከትውልድ ወደትውልድ በኣንድ ኣከባቢ በመኖር ብቻ ብሄረተኝነትን ይሰማሃል ማለት ይቻላል።

የሶሻል ሳይንስ ሙሁራን ብሄረተኝነት ተፈጥሮ ሳይሆን ልማድ ወይም ባህል ነው ይላሉ።ኣብዛኛው ቤረተኝነት ሆነ ተብሎ የሚያድግ ነው ይላሉ።ቀጥሎውም ብሄረተኝነት የሚመነጨው ኋላቀር ከሆኑት ጠባቦች ነው ይላሉ።በተጨማሪ  ሙሁራኖቹ እንደሚሉት ጠባብ ብሄረተኝነት የሚያንጸባርቁት ከተማ ቀመስ ባልሆኑት በብዛት ይታያል ይላሉ።በተጨማሪ  ብሄረተኛ ዋና ምንጩ ለብዙ ዘመናት በኣንድ ኣከባቢ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚኖሩ ህብረተሰብ ሰበብ እንደሆነ ይተርታሉ።ቀጥሎ ውድድር ያደርጋል።የፖለቲካ ሃይል መብት ይጠይቃል።ብሄረተኝነት ፖለቲካ መልክ በመያዝ ይቀጣጠላል።ኣንዳንድ ኣገሮች በብሄራቸው በሰላም ኣገር መስርተው የሚኖሩ ኣሉ።ኢጣልያ፡ጀርመን እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።እንደነዛ ያላደጉ ኣገሮች በራሳቸው ኣደጋ እያንዣበበ የሚኖሩ ብዙ ኣገሮች እንዳሉ ግን ለሁላችን ግልጽ ነው።

የ1914 እና 1939 የኢሮፕ ጦርነት ምንጩ ብሄረተኝነት ነው።ሌላ ቀርቶ ብዙ ሰዎች የእስራኤል ህልውናም ባለው ኣካሄድ ኣይቀጥልም ይላሉ።ምክንያቱ እስራኤል ራስዋ ኣናሳ ብሄር ሁና በፓላስጤን ተውጣለች።እንድያውም ቶንይ ጁድይ (Tony Judy the New York review of Books)እንደጻፉት፡ዓለም በ19ኘው መጨረሻ የጀመረችውን ግስጋሴ ማለትም፡የግለሰብ መብት፡ዓለም ኣቀፋዊ መተባበር፡የወሰን መተሳሰር ወዘተ ኣይሁዶች 'የኣይሁድ መንግስት'(Jewish state)ብሎው ወደ ኣሮጌና ወደ በሰበሰ ኋላ ቀር ኣስተሳሰብ መለሱን ይላሉ።ኣሁንም ቢሆን እስራኤል እንደምንም ብላ  ከፓላስጥኤን ያላትን ችግር ፈትታ ኣብራ ካልኖረች በያዘችው ኣሮጌ ስርዓት መቀጠል ኣይቻልም ይላሉ ብዙ ደፋር ሙሁራን።

ዘረኝነት የሚቀትሎው ክፍለዘመንም እንደሚቀጥል ግልጽ ነው።ሰው እየተማረ፡እያደገ፡ወደ ከተማ እየገባ ሲሄድ፡ፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያድግ፡የልጅ መውለድ ቅነሳ የኤኮኖሚ መሻሻል ከሁሉም ብሄር  ከኣንድ ኣከባቢ ወደሌላ ኣከባቢ እመግረት በማድረግ ወዘተ የሚያጋጥምን ችግሮች መቀነስ ይቻላል።

ብሄረተኝነት ቀላል መፍትሄ ወይም መልስ የለዉም።በየቋንቋውንና በየክልሉ በመገንጠል ዓለምን ያናውጣል።ኣገሮችን መገናጣጠልዓለም ወደ ቀጣይ ቀውሲ ያስገባት እንጂ መፍትሄ ኣይሆንም የሚሉ በኣንድ በኩል ሲኖሩ፡ሌሎቹ ደግሞ የብሄሮችን መብት በመስጠት የየራሳቸው ኣገሮች መመስረት እንደ መፍትሄ የሚያዩት ኣሉ።የብሄር ልዩነት መኖሩን መደበቅ ኣይቻልም፡ ስለሆነም የመገንጠል መብት መስጠት ጥሩ ኣማራጭ ነው የሚሉ ሙሁራን እንደ መፍትሄ ነው የሚሉ ኣሉ።ጥሩ ኣማራጭ ነውም ይላሉ። በሌሎች ሙሁራን ደግሞ የመብት ጠያቂይዎች ጥያቅያቸው ኣጥጋቢ መልስ በመስጠት ኣብሮ በፌዳራሊዝም መኖር ለሁሉም ወገን ጠቃሚ ነው ይላሉ።እውነትነት ያለው ቢመስልም በሁሉም በኩል ብዙ ኣቅም ያስፈልጋል።የሰው ሃይል፡የገንዘብ ኣቅም፡የህግ ሙሁራን፡ፍትህ፡እኩልነት፡ፍትሃዊ የሃፍት መከፋፈል፡ሚዛናዊ ዳኝነት ወዘተ ያስፈልጋል።ይህን ካልተማላ ግን ዞሮ-ዞሮ ታጥቦ ጭቃ ነው።ግጭቱ ቀጣይ ይሆናል።ሁለቱ ኣመለካከት መበታተንና ኣብሮ ችግሮችን እንዳሉ ይዞ መኖር ውጤታቸው ያው ነው እኩል ኣማራጭ ነው።የመፍትሄ ሃሳብ 50/50 ናቸው እንጂ የብሄሮችን ግጭቶች ጨርሶ ኣያጠፋውም።የብሄሮች ግጭት ሃኪም ያልተገኘለት የሰው ልጅ ቁስል ነው።የኣንድ ኣገር ህዝብ በፖለቲካ፡በኤኮኖሚ በእኩል የሚመራ ስርዓት ቢገኝ ተመራጭ ሊሆን ይችላል እንጂ ፍጹም መፍትሄን ሊሆን ግን ኣይችልም።